ቀን12/12/2010 ዓ/ም

# የቦምቡ ነገር !

እናንተየ ስውል ሳድር ብዙ ነገሮች ይገርሙኝና ግርምቴ ለብቻየ አላልቅ ሲለኝ ያለ ልማዴ በአጭር ግዜና በአጭር ፅሁፍ ተሎ ተሎ ለመምጣት ፈለግሁኝና ይኸው ዛሬ ትንሽ ነገር ግን ከአንድ አጀንዳ በላይ የሆነች ነገር ይዤ መጣሁ። ከዚህ በኃላም አጫጭር ጉዳዮች ይዤ ተሎ ተሎ የምከሰት ይመስለኛል። “የለውጥ” መሪዎቻችን ዝም ብሎ የሚሰማ፣ ዝም ብሎ የሚያይ፣ ዝም ብሎ የሚያምን ፣ዝም ብሎ የሚያጨበጭብና ተነስ ሲሉትም ዝም ብሎ የሚነሳ ህዝብ መፈጠሩ ሲያረጋግጡ አሁን አሁን መርን የለቀቀ ነገር በማድረግ ለህዝቡ ያላቸው ገደብ የለሽ ንቀት በማሳየት ላይ ይገኛሉ።

በዚህ አገር በየቀኑ ተገርሜ የማልጨርሳቸው ብዙ በጣም ብዙ አስገራሚም አሳዛኝም ነገሮች እየተከሰቱ ናቸው።መሰረታዊ የሚባሉ የህገ-መንግስት ድንጋጌዎች እንኳንስ በግለ ሰብ በፓርላማም ቢሆን መቀየር የማይችሉት በግል ትእዛዝ ፈርሰው ማየት፣የፌዴራል መንግስት አወቃቀር ፍፁም በተፃረረ መልኩ በክልሎች ሙሉ በሙሉ ጣልቃ በመግባት ህገመንግስቱን በሚፃረር መልኩ መንግስትን እስከመቀየር መሄድ፣ከፍተኛ አመራሮችን መቀየር፣ የአንድ ብሔር የበላይነት ታግለን ነው ለውጡ ያመጣነው ብለው በሚደሰኩሩበት አንደበት ሳይውሉ ሳያድሩ ይህንኑ ያወገዙት ነገር ሲያደርጉ ማየት፣ አማራ የትግል አጋራችን ነው እያሉ በክልላችን እየመጡ በሚያወሩበት አንደበት ከባህርዳር መልስ በማህበራዊ ሚድያና በተግባር ፀረ-አማራ ሃሳብና ተግባራት ማከናወን፣ የመደመርና የይቅርታ ዘመን እንደሆነ እየሰበኩ በተመሳሳይ መድረክ ጥላቻና መቀነስን የሚሰብኩ ንግግሮች እያስፋፉ መምጣት፣ አንዴ “እኛ ኢህአዴጎች” እያሉ ድርጅቱን ማሞካሸት ሌላ ግዜ ኢህአዴግ አለ የምትሉ ካላቹ እስኪ በመላ አገሪቱ ፈልጉና አምጥሉኝ የሚል መግለጫ መስጠት ፣በአገራዊ አንድነትና ፍቅር ስም ኢትዮጵያን በማዳከም በግላጭ አንድን ክልል የሚያጎለብቱ ተግባራት ማከናወን፣በኦሮምኛ የሚናገሩት ሌላ የአማርኛ ዲስኩራቸው ሌላ፣ከአንድ መሪ ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከአንድ ወር የተናገሩት ረስተው ዛሬ ፍፁም ተቃራኒ ሃሳብ ያለ ምንም መሽማቀቅ ማቅረብን፣ በአገራችን ብዙም ባህላችን ባልሆነ መልኩ ለግል ስብእናህ የሚገነቡ አረፍተነገሮች መጠቀምን፣ ከሁሉም በላይ እጅግ አስገራሚው ነገር ከሌሎች የውጭ ኃይሎች ጋር እንዳውም ኢትዮጵያ ስትፈርስ ነው የኛ ብሔራዊ ጥቅም የሚረጋገጠው ብለው የሚያምኑና ለዚህም እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ቀዳሚ ተግባራቸው አድርገው ከሚንቀሳቀሱ አገራትም ጭምር በማበር የአገርንና የህዝብን ጥቅም መሸጥንና ህዝቡ ለዚህም ጭምር እያጨበጨበ መቀጠሉ ወዘተ እያሉ ብዙ መዘርዘር ይቻላል።

የዛሬ ፅሁፌ መነሻ የሆነኝ ግን ከሰኔ 16 የቦምብ ጥቃት ጋር በተያያዘ እየተሰራ ያለ ድራማ ነው።የሞያ ግንኙነቴ በፈጠረው አጋጣሚ ዘግይቶም ቢሆን ከአንድ በጉዳዩ ያለ የህግ ባለሞያ የተረዳሁት ነገር ሲሆን ተስፋዮ ኡርጌ ወይም ኦርጌ (የአባቱ ስም በትክክል ካልጠራሁት ይቅርታ) የተባለ የደህንነት ሰው የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ነው። ኃላፊነታቹ አልተዋጣችሁም ተብለው ከታሰሩት የፀጥታ ሰዎች አንዱ ሲሆን የዚህ ሰው መታሰር ዋና ሚስጥር ተስፋዮ በመስራቤቱ ከቆየባቸው ከ20 በላይ አመታት በሙሉ የሰራው በኦነግ ዙርያ ሲሆን በርካታ የሽብር ቡድኑ አባላት እንዲያዙና በህግ እንዲጠየቁ ያደረገ ሰው ነው።ከዚህ በፊት ኦሮሞ ሆነህ የኦሮሞ ትግል የገደልክ ተብሎ ተደጋጋሚ ዛቻ ሲደርስበት የነበረ ሰው መሆኑንና ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም እንዲታሰር ከተደረገ በኃላ ጉዳዩ ለብዙ ነገር ይጠቅማቸው ዘንድ አበከረው ሰሩበት።እናም ተስፋዮ ለብዙ የኦሮሞ ተወላጆች በደል ፈፅመዋል የኦነግ የኦሮሞ ትግል ጎድቷል የተባለ ሰው ስለሆነ በዚህ አጋጣሚ ሒሳቡ ማግኘት ስላለበት አጀንዳውና የክስ መዝገቡ ተቀይሮ በቸልተኝነት ኃላፊነትህ ያለመወጣት የክስ መዝገብ ወደ ዋና የሽብር ተግባር አስፈፃሚ እንዲዞር በማድርግ እንዲከሰስ ተደረገ።በዚህ ልክ የብቀላ ቅጣቱን ያገኛል።ይህ አንዱ ሲሆን ዋናው ነገር ግን ተስፋየን መሸጋገርያ በማድረግ አልተቀበሉኝም፣ አላከበሩኝም እንዲሁም በሰላም አያኖሩኝም ወደተባሉት የፈረደባቸው ህዋሃቶችን ለማስተሳሰር ተስቦበት እየተሰራ መሆኑ በጣም ታማኝ ከሚባል የውስጥ ሰው መስማት መቻሌ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይቅርና ስለፈፃሚው አካል ስለ ፍፃሜው እንኳን ሙሉ ኢንፎርሜሽን ባልተገኘበት ሁኔታ ግብዝነቱ በሚያረጋግጥ መልኩ ቦምቡ ያፈነዱት የተሸነፉ ናቸው ብሎ ለህዝብ ያወጀው ውንጀላ አዋጅ እንዴት ዝም ብሎ ይታለፍ የሚል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አሁን እየተከተሉት ላለው ህዋሃትን የማዳከምና ከተቻለም የማጥፋት ስራ የግድ መተሳሰር ያለበት በመሆኑ ነው።እናማ የተስፋይ ጎርጌ የጆኬር(አጫዋች) ካርታ የተፈለገው ለተሰፋዬ ተልእኮ የሰጠው አሊቃው የነበረ ጌታቸው እንደሆነ በማስተሳሰር ለህዝቡ በመግለፅ እውነትም እነዚህ ሰዎች አድርገውታል ተብለው እንዲወገዙና አሁን በብዙ የአገራችን አከባቢዎች እያጋጠሙ ያሉ ግጭቶችም በአብይና አመራሩ ድክመት ሳይሆን በእነዚህ ሰዎች ፀረ-ሰላምነት ነው የሚል መልእክት ለማስተላለፍ ነው።በዚህም ህዋህትን ሙሉ በሙሉ ከህዝብ በመነጠል ሰላም እንድናገኝ በነዚህ ሰዎች ላይ እርምጃ ይወሰድልን የሚል ጥያቄ እንዲበራከት አድርገህ በህዝባችን ጥያቄ መሰረት ህዋሃት ከኢህአዴግ እንዲባረር ከማድረግ ጀምሮ ያለ ፖለቲካዊ

እርምጃና ሌሎች ህጋዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያለመ መሆኑ ነው።ለዚህም ህዝቡ ትኩረት እንዲሰጠው ለማስቻል ተስፋየ ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ብቻ ሳይሆን ባልቀረበባቸው ቀናትም ጭምር ፖሊስ አስታወቀ እየተባለ በመንግስት ሚድያ አጀንዳ ተደርጎ እየቀረበ ነው።የኛ ስራ እንደሆነ ሁሉም ማስማት፣ሁሉም ማየት፣ሁሉም ማመንና ሁሉም መደገፍ መሆኑ እየታየ ስለሆነ እስኪ አብረን እንጠብቅ።

አብዛኛው ሃሳቤ ከዚህ ቀደም በነበሩ ፅሁፎቼ የገለፅኩት በመሆኑ ዛሬ ብዙ አላወራም።አንዳንድ ያልገቡኝ ጥያቄዎች ብጠይቅ ቅር እንደማትሰኙብኝ በመተማመን ጥያቄዎቼ ላቅርብ ።አፋሮች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በኤርትራ እየተደረገ ያለ የሰላም ውይይት እኛ ለምን አልተሳተፍንም ? የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡ አሁን እየተሰራ ያለው የፌዴራል ጉዳይ ነው እናንተን አይመለከትም የሚል መልስ ሲሰጥ ሁላችንም ሰምተናል።ታድያ ሱዳን ላይ አቶ ገዱ፣ኬንያ፣የተባበሩት አረብ ኢሜሬቶችና አሜሪካ አቶ ለማ እንዲሁም ጅቡቲ አብድሌን ይዘው የሄዱት የየክልሎቹ ጉዳይ ለማስፈፀም ነበርን? ከዚህ ጋር ተያይዞ ሁሉም ነገር ክፍት ሆኖ ሳለ በድምበር፣በቤተሰብነትና በብዙ ነገር የተሳሰሩ የሁለቱ ክልል ህዝቦች ለማገናኘትና ድንበሩ አለመከፈቱ ለምን ይሆን? ከሰላም ስምምነቱ በኃላ በቅርቡ በኤርትራና በአብይ ወያኔን ታርጌት ያደረጉ ንግግሮች እየተዘወተሩ መምጣታቸው፣ሰራዊት ከድንበሩ የማንሳት እንቅስቃሴ በሙሉ ለእውነተኛ ሰላም ይሆን?ወይስ? ኦህዴድ፣አራቱ ወይም አምስቱ ኦነጎች ጆሃርና ቄሮ የተለያየ አላማ ግብና መዳረሻ ያላቸው ኃይሎች ናቸው ወይስ በአንድ ፊልም ለአንድ አላማና ግብ የተለያየ ገፀ-ባህሪ ተሰጥቷቸው የሚጫወቱ ተዋናዮች? ይህ እንዳለ ሆኖ የግል ዝናና ክብር ከማስጠበቅ አንፃር ለማና አብይ ይተማመናሉን? ለምንድነው ምንም ስሜት በማይሰጥና ምክንያታዊ ባልሆነ ሁኔታ አብይ ለማን እንደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በየሄደበት አገር ይዞት እየዞረ ያለና አሁንም ወደሌላ አገር ይዞት ለመጓዝ እየተዘጋጀ ያለው? ብአዴን ግን ለምን ረዳት ተዋናይ ሆነ? ውይ ዋናው ነገር ረስቸው።ለምን ይሆን እነ አብይ ወደ ስልጣን ከመጡ በኃላ አገራችን ከፀጥታ ችግር አልፎ ወደ መበታተን እያቀናች ያለችው? ብቻ እየተባለ ማለቅያ የሌላቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ ።መልስ ያለው ሰው ካለ፣አስተያየት መስጠት ለፈለገና ለመሳሰሉት ጉዳዮች የተለመደው አድራሻዮ መጠቀም ይቻላል።

ኢ-ሜይል agerawiguday@gmail.com

ፌስ ቡክ selamwerq huluager ያገናኙን።